UNITY FOR HUMAN RIGHTS & DEMOCRACY
7 Woodmount Ave Toronto, Ontario, M4C 1X4
Telephone No. 416 422 2962 Email. unityforhumanrights@gmail.com
www.andnettoronto.blogspot.com
A Canadian Human Rights Advocacy Organization

June 12, 2009

# እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል።

በቶሮንቶ ቅንጅት የኢትዮጵያ የባህልና የዕርዳታ ድርጅት በሚል መጠሪያ የሚታወቀው አካል በአንዳንድ ድረ-ገጾችና የአባላት ስብሰባዎች ላይ ስያሜዬን በፍርድ ቤት ረትቼ ስላስመለስኩ ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ ብሎ ከበሮ ሲደልቅ ሰንበቷል:: አበው እንደሚሉት እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና እውነቱ ሊነገር ይገባል በሚል ይህችን መጣጥፍ ለአንባቢ አቅርበናል። በተለያየ መልክ ሲነዙ ለነበረው የማወናበጃ ፕሮፖጋንዳ መነሻ የሆነው የድርጅቱ ጥቂት የአመራር አባላት የቀረውን የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ሳያማክሩና አዎንታዊ ምላሽ ሳያገኙ ብዙ ሺህ ዶላር ስደተኛው በተለይ ከ1997 አ .ም ጀምሮ ለትግሉ ማጠናከሪያና በወያኔ ታጣቂዎች ለሞቱ፣ ለታሰሩና፣ ለተሰደዱ መርጃ እንዲሆን ያዋጣዉን ፍሬ ከርሲኪ ለሆነ ክስ ስላዋሉና ይህ ጉዳይ ደግሞ ውሎ አድሮ ገንዘቡን በዋጡት አባላትና ደጋፊዎች ሊያስጠይቅ እንደሚችል ስለተረዱ መውጫ ቀዳዳ ለማግኘት እንደ መሸፈኛ ፕሮፖጋንዳ ተጠቅመውበታል። ወያኔን ገጥመው እዳሸነፉና ገንዘቡንም ለዚሁ ስለዋሉ የሂሳብ ምርመራም ሆነ ጥያቄ ማንም ሰው እዳያቀርብ ለመከላከል የተደረገ መሠሪ ፕሮፓጋንዳ ነው።

ስለዚህ እኛም ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ እንደሚሉት ነውና የነገሩ መነሻ እንዴት እንደነበረ፣ አገር ወዳድና እኛንም እነሱንም ሲደግፍ የነበረው ህዝብና በተለይ ምንም እዳያውቁ የተደረጉት አባሎቻቸው እንዲያውቁት ለማድረግና በተጨማሪም የዚህ ድርጅት ጥቂት የአመራር አባላትን ባህሪይ፣ የአመለካከት አድማስ፣ ስነልቦነዊ አስተሳሰብ በጥቂቱም ቢሆን ለአንባቢ ለማሳወቅ ይረዳል ብለን ስላሰብን ጉዳዩን እንደሚከተለው እናቀርባልን።

ሀ) ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ከመመሥረቱ ከስድስት ወር በፊት ቀደም ብሎ መኢአድ ተብሎ በሚጠራው ጽ/ቤት አባላትና ደጋፊዎች በመሆን በኢትዮጵያ የሚደረገውን ትግል ማገዝ ጀመርን። በተለይም ቅንጅት ተመስርቶ በ1997 ምርጫ ለመካፈል ወስኖ ቅስቀሳ ያደርግ በነበረበት ወቅት ለትግሉ ማካሄጃ ገንዘብ በማሰባሰብና ቅስቀሳ በማድረግ ብዙ ተሳትፎ አድረገናል። በግንቦት 7፤ 1997 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ ቅንጅት አሸናፊ በመሆኑ ወያኔ የዲሞክራሲ ሂደቱን በጠመንጃ ኃይል በመቀልበስ የብዙ ንጹሃን ዜጎች ህይወት በማጥፋት፣ በሽዎች በሚቆጠሩት ላይ የአካል ጉዳት በማድረስ፤ መቶ ሺዎች የሚሆኑትን ደግሞ በእሥር ቤት በማጎር ያደረሰውን ሰቆቃ የአለም ሕብረተሰብ እንዲያውቀው ለማድረግ የትግል አስተዋጽዎአችንን አጠናክረን በመቀጠል፡ በየሁለት ሳምንት ህዝባዊ ስብሰባ እንዲደረግና ገንዘብ እንዲዋጣ፤ ሰላማዊ ሰለፍ እንዲከሄድ፤ እንዲሁም የተለያዩ የዲፕሎማሲ ዘማቻዎች እንዲደረጉ በመርዳት ትግሉን በማፋፋም ረድተናል።

ብዙዎቻችን በወቅቱ አትኩሮታችን በጣም አንገብጋቢ በነበረው በታሠሩት የቅንጅት አባላትና እነሰርሱን ያሰቃይ በነበረው ወያኔ ላይ ስለነበረ ዞር ብለን የነበርንበት ድርጅት መሪዎች ከ14 ዓመት በላይ በአባላት ሳይመረጡ እነርሱ ብቻ እየተመራረጡ በመጀመሪያ በመአህድ፣ ከዚያም በመኢአድ፣ ቀጥሎም በቅንጅት ስም በመለዋወጥ መቆየታቸውንና የረባ የመተዳደሪያ ደንብ እንኳን የሌላቸው እንደሆነ፤ የሚሰበሰበው ገንዘብ በማን ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ እንደሚገባ አትኩሮት ሳንሰጥ በኢትዮጵያዊ እምነት ብቻ በብዙ አሥር ሺዎች የካናዳ ዶላር የሚቆጠር በማሰባሰብ ገቢ እንዲሆን አድርገናል። (ድርጅቱ እስካሁን የኦዲት ሪፖርት አቅርቦ አያውቅም)። ታዲያ እ.አ.አ በግንቦት ወር 2006 ዓ.ም እንድ ዓይናችንን እንድንከፍትና እነድንጠራጠር እራስችንንም ሆነ እነርሱን እንድንጠይቅ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጠረ።

ይኸውም የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ሲቋቋም በዚህ ጉዳይ ላይ ጥቂት የሆኑ የድርጅቱ የአመራር አባላት ሌላውን ሳያማክሩና ስብሰባ ሳይጠሩ አቋም ያዙ። ይኸውም እኛ ዓለም አቀፍ አመራሩን አንቀበልም። የአመራሩ አባላት የወያኔ አባላት ናቸው በማለት ተቃውሞአቸውን በተለያየ መልክ ገለጹ።

በዚህም የተነሳ ብዙ አባላት ቅሬታቸውን ማንሳት ጀመሩ። ስብሰባም እንዲጠራ በስልክ እየደወሉ መጠየቅ ጀመሩ። ለህዝቡ ጥያቄ ምንም መልስ ሳይሰጡ ከስድስት ወር በላይ በራቸውን ዘግተው ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርጉ ተቀመጡ። በመጨረሻም በሽማግሌ እንዲጠየቁ ተደርጎ የመጀመሪያ ስብሰባ እ.አ.አ. በኖቬምበር 17፣ 2006 አካሄድን፡

በዚህም ስብሰባ የሚከተሉትን ዋና ጉዳዮች አንስተን ተወያየን።

- የድርጅቱ መሪዎች አባላቱንና ደጋፊዎችን ሳያወያዩና ሳያስወስኑ፣ የቅንጅት ዓለማቀፍ አመራርን መቋቋም በሚመለከት የወሰዱት እርምጃ ህዝብን ሊከፋፍል የሚችል ወገናዊና ከኢትዮጵያዊ ስነምግባረ ውጭ ስድብና የስም ማጥፋት ዘመቻ የተሞላበት በመሆኑ እንዳሳዘነን፤
- ከላይ ለተጠቀሰው እርምጃ ምክንያት የሆነው መሪዎቹ በምርጫ ሳይሆን በመሿሿም በስልጣን ላይ በመቆየታቸው ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርጫ እንዲደረግ፤
- ድርጅቱ እንደገና ኢትዮጵያ ያለውን የቅንጅት አመራርን በመከተል በዲሞክራሲያዊና በግልጽነት እንዲሁም ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ እንዲዋቀርና መመሪያ እንዲያወጣ የሚል ሲሆን፣
- በውይይቱ ላይ ላቀረብናቸው ጥያቄዎች የሰጡን ምላሽ የሚያስገርም ነበር። እነሱ የተደራጁት ከአዲስ አበባ ጽ/ቤት በቀጥታ ከአቶ ኃይሉ ሻውል በተሰጠ መመሪያ ስለሆነና ማንኛውም አባልም ሆነ ደጋፊ በዚሁ መመሪያ መሠረት ብቻ ተሳትፎ እንደሚያደርግና የቦርድ አባል ሆኖም ለመመረጥ እነሱ ብቻ ስልጣን እንዳላቸው ቁርጥ አድርገው ነገሩን። ከዚያ በኋላ ነገሩ "አላየህን ግባ በሉት" ስለሆነ ለመጨረሻ ጊዜ በጽሁፍ ዲሴምበር 20/2006 በቶሮንቶና አካባቢው የሚገኙትን ደጋፊዎችና አባላት በመጥራት ውይይት ተደርጎ በኮሚቴ የተረቀቀ መተዳደሪያ ደንብ እንዲጸድቅና መሪዎችም በግልጽና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲመረጡ እንዲያደርጉ ጠየቅን። ለጥያቄአችንም እንደልማዳቸው ጆሮ ዳባ ልበስ በማለታቸው ሁለት ወር ጠብቀን በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም. ቅንጅት ለሰብአዊ መብትና ዲሞክራሲ በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ድርጅት አቋቋምን።

ለ)በአዲስ መንፈስ የታሰሩትን የቅንጅት አባላት ለማስፈታትና በኢትዮጵያ ፍትህና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የምናደርገውን ትግል በሰፊው ተያያዝን። በዚህም የተነሳ የብዙኃን ኢትዮጵያዊያንን ቀልብ ለመሳብና አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ለማሳደግ ቻልን። ይህም ሥራችን በወንድሞቻችን ቅናትን በውስጣቸውም መንገብገብና ቁጭትን ፈጠረባቸው። በበቀልም ስሜት ተነሳስተው ክስ መሠረቱብን።

ሐ)የክሱ መጥሪያ ሲደርሰን ለማመን ከብዶን ነበር። ከመገረምም አልፎ የእፍረት ስሜት አሳደረብን። ምክንያቱም ትናንት አብረን ለአንድ ዓለማ የተሰለፍን ሰዎች ዛሬ እርስ በርስ እየተናከስን ለጠላቶቻችን መሳቂያና መሳለቂያ ከመሆን አልፎ አገራችንን ከወያኔ መንጋጋ እንድናወጣ እርዱን እያልን በየግዜው የምንጨቀጭቃቸው የካናዳ መሪዎች ለምን ተከፋፈላችሁ ቢሉን ምን መልስ ልንሰጥ እንደምንችል ማሰብ ጀመርን። ከሁሉም በላይ ስደተኛው ወገናችን ከአፉ ነጥቆ ለትግሉ ይረዳል ብሎ ለነረሱም ለኛም የሚሰጠውን ገንዘብ ለፈረንጅ ጠበቃ ለመስጠት መዘጋጀታችን ይበልጥ አቃጠለን። ወዲያው እንደ መፍትሄ የወስድነው በግዜው የቅንጅት ፕሬዚዴንት የሆኑትን አቶ ኃይሉ ሻወልን ማነጋገርና ክሱን እንዲያስቆሙልን መጠየቅ ነበር። በዚህም መሰረት በተከታታይ በስልክ ብዙ ገዜ ጠይቀን እጥጋቢ መልስ ባለማግኘታችን ሁለት ጊዜ በደብዳቤ ልመናችንን አቅርብን። ታዲያ "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ሆነና ምላሽ ባለማግኘታችን ለክሱ መልስ ለመስጠት እንድንችል ሶስት ቀን ሲቀረን የህግ ባለሙያ ተነጋግረን ያዝን።

7 Woodmount Ave Toronto, Ontario, M4C 1X4
Telephone No. 416 422 2962 Email. unityforhumanrights@gmail.com
www.andnettoronto.blogspot.com
A Canadian Human Rights Advocacy Organization

መ) መካሰሳችንን የሰሙ የቶሮንቶ ኗሪዎች በጉዳዩ በማዘናቸው በመካከላችን ሽማግሌዎች እንዲገቡና ጉዳዩን በጥሞና እንዲመለከቱ ገፋፍተው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ፣ ከኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ተወካይ ዶ/ር ቡሻ ታዓና ሁለት የኮሙዩኒቲ አባላት ደ/ር ኃይሌ ፋንታና አቶ መላኩ ስዩም ሆነው ጉዳዩን ለማየትና ውሳኔ ለመስጠት ከኦክቶበር 20/2007 ጀምሮ ጉዳዩን መመልከት ቢጀምሩም ለስብሰባ ጥሪ ሲያቀርቡ እኛ በሙሉ ልባችን ደግፈን በተከታታይ በተጠራነው ስብሰባ ስንገኝ እነርሱ በአንድ ስብሰባ ላይ ብቻ በመገኘት በቀሩት ላይ ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ ስለሆነ እልባት የሚያገኘውም በዚያው ነው በማለት እምቢተኝነታቸውን ስለገለጹ ሽማግሌዎቹ እኛን በማመስገንና እነርሱም ባለመሳተፋቸው በማዘን በደብዳቤ መግለጫ ለቶሮንቶ ኮሚኒቲ  አባላት ሰጡ።

እኛም ሽማግሌዎቹን ስለጥረታቸው አመስግነን ለወንድሞቻችን ደግሞ ቅን ልቦናና  መልካም አስተሳሰብ እንዲሰጣቸው ገልጸን እንግዲህ በፈለጉት መገድ ይቀጡሉ ብለን ተውን።

ሠ) ከዚህ ቀጥሎ አንድ ለተመልካች የሚያስገርም ነገርና  የድርጅቱን ጥቂት መሪዎች ባህሪና አስተሳሰብ የሚገልጽ ጉዳይ ተፈጸመ። በመጀመሪያ ክሱን መስርተው የነበረው በቶሮንቶ፣ በዋተርሉ፣ በካልጋሪ፣ በዊኒፔግና በቫንኮቨር በተቋቋሙ ቅንጅት ጽ/ቤቶች ላይ ሲሆን በዚህ ክስ አካሄድ ብዙ ወጪ አውጥተው ሳለ በመሐል ተነስተው የክሳችንን ጭብጥ ለመለወጥ ስለምንፈልግ $2200.00 እንከፈላችሁና ተባበሩን ብለው በጠበቃችን በኩል ጠየቁን እኛም እየተገረምን ስለጉዳዩም ከነርሱ የበለጠ ጠለቅ ያለ ግንዛቤና ይህ ጉዳይ እልባት ሳያገኝ ለዓመታት ብሎም ለዘመናት መቆየት እንደሚችል ስለተረዳን ጉዳዩን በደስታ እሽ ስጡን ብለን ገነዘቡን ተቀብለን ለጠበቃችን የክፍያ ማሚያ አደረግን። አሻሽለው ያመጡት ክስ ደግሞ የቶሮንቶን ለቅንጀትና ለሰብአዊ መብትና ዲሞክራሲንና የቅንጅት ካናዳ ካውንስልን የቦርድ አባላትን በግል  በስም በመዘርዘር  መክሰስ ነበር።

ረ) የቅንጅት ስምና አርማ በወያኔ ለደጋፊዎቹ ለአየለ ጫሚሶና ለልደቱ አያሌው ሲከፋፈል በሀገር ቤት ተለያይተው የነበሩት በኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመሩት ድርጅቶች ስማቸውን ለመለወጥ ሲገደዱ፤ በዚሁ መሠረት የቅንጅት ወራሽና አባዛኛዎቹን የቀድሞ የቅንጅት አመራር አባላት የመሰረቱት ፓርቲ ስሙን እንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ብሎ በመሰየሙ እኛም ከእንግዲህ ቅንጅት ለእኛ የመታገያ ስም ሊሆን እንደማይችል በመገንዘብና በተጨማሪም ብዙ አባላትም ቅንጅት የሚለው በሀገር ቤት የወያኔ ደጋፊዎች መጠሪያ ስም እንጅ የወያኔ ተቃዋሚዎች ስላልሆነና እኛ ደግሞ አገር ቤት ያለው የቅንጅት ወራሽ የሆነው የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች ከሆን እዚህም በውጭ ሀገር በዚህ ስም የሚጠሩ የወያኔ ድርጅቶች ከመቋቋማቸው በፊት ለወንድሞቻችን ከፈለጉት ለምን እንተውላቸውም ብለን ወሰነን በጠበቃችን በኩል ጥያቄ እንዲቀርብላቸው አደረግን። ይህንን ሃሳብ ስናቀርብላቸው የፈራንና ምናልባትም ገንዘብ ያጣን ስለመሰላቸው የለም ስሙን ብቻ ሳይሆን በቅንጀት ስም ባለፉት ሁለት ዓመታት የተሰበሰበውን $78000 ዶላር(ወ/ት ብርቱካን ቶሮንቶ በመጣች ጊዜ የተዋጣውንና ለድርጅቱ የተላከውን ጨምሮ)ና እንዲሁም ቅንጅት በተሰኘው የንግድ ምልክት በመጠቀማችን እንሱ ሊያገኑት የሚገባውና ያጡትን $50000.00 ካስ ጭምር እዲሰጠን ብለው መልስ ሰጡን።

እኛም ስሙንም ሆነ አርማውን ሳትከፍሉበት በነጻ ያገኛችሁት ስለሆነ በነጻ ውሰዱት ያለዚያ በጀመራችሁት መንገድ ቀጥሉበት ብለን ተውናቸው።

ሰ) ከስድሰት ወር በኋላ ካዝናቸው ታሚጠጠ። ለጠበቃ የሚከፈል ጠፋ፤ ጉዳዩ ረጂም ጊዜ የሚወስድና እጅግ ብዙ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑን ተረዱት ስለዚህ ሰሙን በመውሰድ እንደሚስማሙ ለጠበቃችን ገለጹለት እኛም እሺ ምን ጎሎን በፊትም ብለን ነበር። ታዲያ የምንስማማበትን ሁኔታ አርቅቃችሁ  አቅርቡልን አልናቸው። መጀመሪያ ባቀረቡት ረቂቅ ላይ በቅንጅት ስም የተጠቀምንበትን ማንኛውንም ዶኩሜንት ለነርሱ እንድናስረክብ  አርቅቀው አቀረቡ።

# UNITY FOR HUMAN RIGHTS & DEMOCRACY

7 Woodmount Ave Toronto, Ontario, M4C 1X4
Telephone No. 416 422 2962 Email. unityforhumanrights@gmail.com
www.andnettoronto.blogspot.com
A Canadian Human Rights Advocacy Organization


እኛም ከስሙና አርማው በስተቀር ማለት “የቄሳርን ለቄሳር” በሚለው አባባል መሠረት እንዲወስዱና ሌላ ገንዘብ፣ ዶኩዩመንት ሌላም ነገር ሊጠይቁ እንደማይችሉ አደረግን አርቅቀን ሰጥተን በዚሁ ላይ የጋራ ሰምምነት አድርገን፣ ስምነታችንም በፍረድ ቤት እንዲጸድቅ ተደረገ።

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ጉዳዩ ፍረፈርስኪ የነበረና ለረጅም አመታት ያለዉሳኔ ሊቆይና ብዙ ውጪና ጊዜን የሚጠይቅ ጉዳይ እንደሆነና ይህ ደግሞ በአባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ጥያቄን፣ ጥላቻንና ከድርጅት መራቅን የሚያስከትል መሆኑን ባለማወቅም ሆነ በትእቢት የተከናወነና በመጨረሻም ውጤቱ  ጥቂት የአመራር አባላት ብቻ ይዞ መቅረትን አስከትሎባቸዋል። በእኛ በኩል ጉዳዩን በብልህነትና በአርቆ አስተዋይነት ስለያዝነውና አትኩሮታችንም ያነጣጠረው በወያኔ ላይ ብቻ እንጂ በወንድሞቻችን ላይ ስላልነበረ የገንዘብና የሞራል እርዳታ ከብዙዎች አግኝተናል።

በዚህ አጋጣሚ እኛ ለጠበቃ በሁለት ዓመት ጊዜ አንድም ቀን ፍርድ ቤት ሳንቀርብ $13000.00 አውጥተናል። እነርሱ ለኛ ከከፈሉትና ጉዳዩን ቀደም ብለውም በስፋት ይዘውት ስለነበረ እኛ ከከፈልነው በእጥፍ ከፍለዋል ብለን እንገምታለን። ከዚህ የተለየ ነው ካሉ የከፈሉትን መጠንና ገንዘቡንም ከየት እንዳገኙ ሊያቀርቡ ይገባል እንላለን።

እኛ የከፈልነው ገንዘብ ከየት መጣ ለሚለው እንደሚከተለው እናቀርባለን፦

በሰሜን አሜሪካ ያሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን 7300.00 ዶላር ሲረዱን $2.2000 ከሳሾች ክሳቸውን ለማሻሻል የከፈሉን ሲሆን የተቀረው በጠንካራ አባሎቻችን ተሸፍኗል። ስለዚህ በገንዘብና በሞራል ከጎናችን ለቆሙት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን። በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዩን በሀጋራችን ወግና ልማድ መሠረት በሽምግልና እንዲያልቅ ለጣሩት ሁል ምስጋናችን ይድረሳቸው።

በትግላችን ህዝባችን ነጻነቱንና መብቱን ይጎናጸፋል